- 19 -

የተዘጉ በሮች እና ያሳወሩን ብሹታዎች

ትናንትና ነበር። የ22 ወር ልጄ የራሱን ነፃነት ለማወጅ ሲንቀሳቀስ በዐይኔ አየሁት። ከመኪና ወንበሩ መቀመጫ መሐል ከወጣ በኋላ እንደ ትልቅ ልጅ በሩን ለመዝጋት ሞከረ። እኔ የሚሠራውን ሁሉ በቅርበት እከታተለው ነበር። እኔ በሩን እንድዘጋ ብተወው ኖሮ ትንሹ ጭንቅላቱ በግጭት ኣይተርፍም ነበር። አነሳሁትና በሩን እራሴ ዘጋሁት። ድርጊቴ አናደደውና አለቀሰ። እሱ ማድረግ የፈለገውን ነገር ስለከለከልኩት ነበር የተበሣጨው።

ከስተቱን እያየሁኝ የሆነ ሀሳብ ጭንቅላቴ ውስጥ መጣ። በተለይ ከአላህ አንፃር የዚህ ዓይነቱ ነገር በሕይወታችን ውስጥ ሁሌም ያጋጥመናል። እኛ አንድን ነገር ስንፈልግ አላህ ግን ሳይፈልግ ሲቀር እንዴት እንደሚከለከለን አስተዋልኩበት። በተለይ ወጣት ሆነን ሳለ የዚህ ዓይነቱ ነገር በተደጋጋሚ ያጋጥመናል። አንድን ነገር በእጅጉ ፈልገን እኛ በፈለግነው መልኩ ካልተሳካልን ተስፋ እንቆርጣለን፤ እንናደዳለን፣ ከፉኛ እንበሣጫለን። ግና ኋላ ላይ ቆይቶም ቢሆን አለመሳካቱ ለበጎ እንደሆነ ይገለጥናል። እኔ ልጄ እንዳይጎዳ ያደረግኩት ነገር ቢኖር በሩን እንዳይታገለው እሱን መውሰድ ብቻ ነበር። እሱ ግን ለሱ ጥቅም እንደሆነ አልገባውም። በመነጫነጩ መሐል ሆኖ ከትልቅ አደጋ እንዳዳንኩት አያውቅም ነበር። ልጄ ምንም ሳያውቅ በየዋህነቱ እንዳለቀሰው ሁሉ እኛም እንዲሁ ካለቀስንላቸው ነገሮች አላህ እኛን ያዳነበት ሁኔታ ብዙ ነው።

የአውሮፕላን የበረራ ሰዓት ሲያመልጠን፣ ሥራ ስናጣ፣ ካሰብነው ሰው ጋር በትዳር የመጣመር ጉጉታችን ሲከሽፍ ... ሌላም ሌላም ገጠመኝ ሲገጥመን "ይሁን ለበጎ ነው" ብለን ያሰብንበትና ያሳለፍንበት አጋጣሚ ይኖር ይሆን!

አላህ (ሱ.ወ.) በቁርኣኑ እንዲህ ይለናል :-

﴿ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلْقِتَالُ وَهُوَ كُرْهٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰٓ أَن تُحِبُّوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ شَرٌّ لَّكُمْ ۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ﴾

«(ከሃዲዎችን) መጋደል እርሱ ለናንተ የተጠላ ሲሆን በናንተ ላይ ተፃፈ። አንዳች ነገርን እርሱ ለናንተ የበለጠ ሲሆን የምትጠሉት መሆናችሁ ተረጋገጠ። አንዳችንም ነገር እርሱ ለናንተ መጥፎ ሲሆን የምትወዱት መሆናችሁ ተረጋገጠ። አላህም (የሚሻላችሁን) ያውቃል፤ ግን እናንተ አታውቁም።»

(አል-በቀራህ : 216)

በርግጥ ከነገሮች ጀርባ ያለውን ሁኔታ አሻግሮ መመልከት ከባድ ነው። እውነት ከሚመስል ስህተት አሻግሮ መመልከት ትልቅ ጥንካሬን ይጠይቃል። እውነታን በጥልቅ መረዳትን ይሻል። ያንን ደግሞ ልንረዳውም ላንረዳውም እንችላለን። ምናልባት በጊዜ ሂደት ካልሆነ በስተቀር እውነታን ቶሎ አናይም። ልጄ እጅግ ከሚፈልገው ነገር እሱን መከልከሌ ለርሱ ጥቅም እንዳለው እንዳልተረዳው ሁሉ ማለት ነው። እኔ አየሁለት እንጂ እሱ ፈጽሞ አላየም። ስለሆነም እኛም የሰው ልጆች እንዲሁ ነን። አምላካችን አላህ (ሱ.ወ.) ከሚያይልን ነገር አንፃር እውር ነን ማለት ነው።

በዚህም የተነሳ ነገሮችን ሳናውቅና በጥልቀት ሳንመረምር በሕይወታችን ውስጥ በተዘጋው በር ላይ እናተኩራለን። የተከፈተልንና አጠገባችን ያለውን አናስተውልም። በአዕምሯችን ውስጥ ያለውን ሰው ማግባት ካልቻልን፤ ከርሱ የተሻለ ሰው ቢመጣ እንኳን ከርሱ ውጭ የመመልከት ሁኔታችን እውር እና ደካማ ነው የምንሆነው። በአንድ በጓጓንለት ሥራ ላይ መቀጠር ካልቻለን ወይም አንድ የምንወደውን ነገር ካጣን፤ ወደኋላ ዞረን ትላልቅ ነገሮችን የማየታችን ሁኔታ ከባድ ነው የሚሆንብን። ብዙን ጊዜ አላህ ነገሮችን የሚወስድብን ከነርሱ በተሻለ ጥሩ ነገር ሊተካልን ነው ብለን አለማሰባችን እንደሚጎዳን ማወቅ አለብን።

አንዳንድ አሳዛኝ ነገሮች በዚህ መልኩ ሊከሠቱ ይችላሉ። አንዳንድ ሰው የሆነ አደጋ ቢደርስበት ልጅ ከማጣት በላይ ሊያሳምመው ይችላል። እነኚህ የሳሳንላቸውና ያንገበገቡን ማጣቶች ሳይቀሩ እኛን ለማዳን እና የተሻለ ነገር ሊሠጡን ነው የሚመጡት ብለን ብናስብ መልካም ነው።

የአንድ የአላህ ባርያ ልጅ የሞተ እንደሆነ አላህ (ሱ.ወ.) ለመላእክቱ እንዲህ ይላል፡- “የባርያዬን ልጅ ወሰዳችሁን?”

መላእክቱም “አዎን” ይላሉ።

አላህም “ የልቡን ፍሬ ወሰዳችሁበትን?” ይላል።

መላእክቱም “አዎን” ይላሉ።

አላህም “ባርያዬ ምን አለ?” ይላቸዋል።

መላእክትም “አላህን አመሰገነ፣ እኛ ለአላህ ነን ወደ አላህ ተመላሾች ነን።” አለ ይሉታል።

አላህም “ለባርያዬ ጀነት ውስጥ ቤት ገንቡለት፤ ስሙንም የምስጋና ቤት” በሉት ይላቸዋል።” (ቲርሚዚ እንደዘገቡት)

አላህ ልጅንም ሆነ የመሣሠለውን አንዳች የምንወደውን ነገር ሲወስድብን የተሻለውን ነገር ሊሠጠን ነው ብለን ማሰብ ይኖርብናል። በዚያ በተወሰደብን ልጅ ምክንያት ከልጃችን

ጋር ዘላለማዊ የሆነውን የአላህ ፀጋ ጀነት ሁሉ ልንገባ እንችላለን። የጀነት ሕይወት ከዚህ ዓለም ሕይወት ፈፅሞ የተለየ ነው። እዚያ ህመም የለ፣ ስጋትም ሆነ ፍራቻ፣ በሽታም ሆነ ሐዘን የለም።

በዚህ ምድራዊ ሕይወት የሚያገኝን ህመም ህመሙ ብቻ ሊታየን አይገባም። አላህ በበሽታም ሆነ በሌሎች በሚያገኙን ችግሮች ምክንያት ከወንጀላችን ያጠራናል። የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከፍተኛ የሆነ ትኩሳት ባገኛቸው ጊዜ "አንድን ሙስሊም የሚያገኘው ማንኛውም ጉዳት፣ ሌላው ቀርቶ እሾህ እንኳን አይወጋውም በዚያ ምክንያት ቅጠል ከዛፍ እንደሚረግፈው ሁሉ አላህ ወንጀሉን ያረገፈለት ቢሆን እንጂ።" ብለዋል። (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

በሌላም ንግግራቸው ሐዘንና ጭንቀትንም እንደሚያካትት የገለፁ ሲሆን "አንድን ሙስሊም መከራ፣ በሽታ፣ ሐዘን፣ ሀሳብ፣ ጉዳት ወይም ጭንቀት ሌላው ቀርቶ እሾህ እንኳን አይወጋውም አላህ በዚያ ምክንያት ወንጀሉን ያረገፈለት ቢሆን እንጂ።" ብለዋል።

ድህነትም እንዲሁ ነው። ድህነትም ጸጋ ነው። ፈተናው ከበዛ ሀብት ፈተናው ያነሰ ድህነት ይሻላል። ሀብታም ያልሆኑ ብዙ ሰዎች ሀብት አለማግኘታቸውን ከጸጋ አይቆጥሩትም። ነገር ግን በቃሩን ዙርያ እንዳሉ ሰዎች ሀብትን ይመኛሉ። ቃሩን በነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) ዘመን የኖረ ሰው ነው። አላህ እጅግ ብዙ ሀብት ሰጠው። የመጋዘን ሀብቱ ቁልፉ ብዛት ብቻውን በራሱ አንድ ሀብት ይሆናል። እናም ይህንን አይተው ሀብት የሌላቸው ሰዎች ቀኑበት። ቁርኣን እንዲህ ይላል:-

﴿ فَخَرَجَ عَلَىٰ قَوْمِهِۦ فِى زِينَتِهِۦ ۖ قَالَ ٱلَّذِينَ يُرِيدُونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا يَٰلَيْتَ لَنَا مِثْلَ مَآ أُوتِىَ قَٰرُونُ إِنَّهُۥ لَذُو حَظٍّ عَظِيمٍ ﴾

«በሕዝቦቹም ላይ በጌጡ ውስጥ ኾኖ ወጣ። እነዚያ ቅርቢቱን ሕይወት የሚፈልጉት፥ ወይ ምኞታችን! ቃሩን የተሰጠው ብጤ ምነው ለኛ በኖረን፤ እርሱ የታላቅ ዕድል ባለቤት ነውና፤ አሉ።» (አል-ቀሶስ : 79)

ቃሩን የሀብቱ ብዛት እንዲንጠባረርና እንዲኩራራ አደረገው። ከማመስገን ይልቅ በአላህ ማመጽን ምርጫው አደረገ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል:-

﴿ فَخَسَفْنَا بِهِۦ وَبِدَارِهِ ٱلْأَرْضَ فَمَا كَانَ لَهُۥ مِن فِئَةٍ يَنصُرُونَهُۥ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلْمُنتَصِرِينَ ﴿٨١﴾ وَأَصْبَحَ ٱلَّذِينَ تَمَنَّوْا۟ مَكَانَهُۥ بِٱلْأَمْسِ يَقُولُونَ وَيْكَأَنَّ ٱللَّهَ يَبْسُطُ ٱلرِّزْقَ لِمَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ وَيَقْدِرُ ۖ لَوْلَآ أَن مَّنَّ ٱللَّهُ عَلَيْنَا لَخَسَفَ بِنَا ۖ وَيْكَأَنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَٰفِرُونَ ﴾

«በርሱም በቤቱም ምድርን ደረባን። ለርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች ምንም አልነበሩትም። ከሚርረዱትም አልነበረም። እነዚያም

በትላንትናው ቀን ስፍራውን ይመኝ የነበሩት "ወይ ጉድ! ለካ አላህ ከባሮቹ ለሚሻው ሰው ሲሳይን ያሰፋል፣ ያጠባልም። አላህ በኛ ላይ (በእምነት) ባልለገሰልን ኖሮ ምድርን በኛ ላይ በገለበጠብን ነበር። ወይ ጉዱ! ከሓዲዎች አይድኑም" የሚሉ ኾነው አነጉ።» (አል-ቀሶስ ፡ 81-82)

የቃሩንን መጨረሻ ካዩ በኋላ እነዚያ የሱን ዓይነት ሀብት ባገኝን ብለው የተመኙት ሁሉ ሀሳባቸውን ቀየሩ። አላህ (ሱ.ወ.) በለገሳቸው ነገር ተብቃቁ፤ አመሰገኑ።

በአል-ከህፍ ምዕራፍ ውስጥ የተነገረን የነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) እና የኸድር ታሪክም ትልቅ ማስተማሪያ ነው። ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ.) ከሰዪድና ከኸድር ጋር በመጓዝ ላይ ሳሉ ኸድር ለሙሳ እንግዳ እና መጥፎ የሆኑ ነገሮችን ያደርጉ ነበር። መጨረሻ ላይ ኸድር ምክንያቱን ባስረዳቸው ጊዜ እኛ ውስጠ ሚስጢራቸውን የማናውቃቸው፤ አላህ ግን በጥበቡና በዕውቀቱ እንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው ነገሮች እንዳሉ ተረዱ። እኛ ላያቸውን ብቻ ነውና የምናየው።

ኸድርና ሙሳ ወደ አንዲት ከተማ በገቡ ጊዜ ኸድር ሰዎች የሚሠሩባትን ጀልባ ሸነቆሩ። ነገሩ ሲታይ ለተመልካች ግራ ያጋባል፣ ያናድዳል። የድሆችን እንጀራ ማግኛ እንዴት ይሰብራል? ያስብላል። ኋላ ላይ ኸድር ለምን ይህን እንዳደረጉ ለሙሳ አስረዷቸው። ይህን ያደረጉት ድሆችን ለመጉዳት ሳይሆን የነርሱን ንብረት ለመከላከልና ጀልባቸውን ለማትረፍ ነበር። አላህ በቁርአኑ ውስጥ ይህንኑ ነግሮናል፡-

﴿ قَالَ هَٰذَا فِرَاقُ بَيْنِي وَبَيْنِكَ ۚ سَأُنَبِّئُكَ بِتَأْوِيلِ مَا لَمْ تَسْتَطِع عَّلَيْهِ صَبْرًا ﴿٧٨﴾ أَمَّا السَّفِينَةُ فَكَانَتْ لِمَسَٰكِينَ يَعْمَلُونَ فِي الْبَحْرِ فَأَرَدتُّ أَنْ أَعِيبَهَا وَكَانَ وَرَاءَهُم مَّلِكٌ يَأْخُذُ كُلَّ سَفِينَةٍ غَصْبًا ﴾

"(ኸድር) አሰ "ይህ በኔና በአንተ መካከል መለያያ ነው። በእርሱ ላይ መታገስን ያልቻልክበትን ፍች እነግርሃለሁ። "መርከቢቱማ በባሕር ለሚሠሩ ምስኪኖች ነበረች:: ከኋላቸውም መርከብን ሁሉ በቅሚያ የሚይዝ ንጉሥ ነበረና፣ (እንዳይቀማቸው) ሳነውራት ፈቀድኩ።" (አል-ከህፍ ፡ 78-79)

ጀልባዋን በመጉዳትና የማትረባ በማስመሰል ኸድር ሊቀማቸው ከነበረው ንጉሥ እጅ የድሆችን ንብረት አተረፉላቸው። አንዳንዴ በሕይወታችን የሚያጋጥሙን ነገሮችም እንዲሁ የዚህ ተመሳሳይ ናቸው። እኛን ለማዳን ሲባል አንዳንድ ነገሮች ይወሰዱብናል። አያለቀስን እንቀማለን። ወይም እኛ ሳንፈልጋቸው ይሠጡናል። ይህ ነው እንግዲህ ከላይ ከመነሻው ያወሳሁላችሁ የ22 ወር ህፃን ልጄ ሁኔታ። እሱ በሩን ሊዘጋ ተንደረደረ። እኔ ደግሞ እንዳይጎዳ በማሰብ ቀድሜው ልጄን አነሳሁት።